Institute of Development & Education for Africa, Inc.

webmaster@africanidea.org 1199 Whitney Ave Suite 523, Hamden, Ct 06511 USA Telephone: 1+203-747-2763 (mobile) 1+203-789-1990 (Office)

# ታሪካችሁን ብታውቁ ምን ያህል አንድ ሕዝብ መሆናችሁን ትገነዘባላችሁ

## ልዩ መልእክት ለኢትዮጵያ ወጣቶች እና ለዩንቨርሲቲ ተማሪዎች

**ገላውዴዎስ ኣርኣያ ዶ/ር September 5, 2018 ነሐሴ ፴ ፪ሺ፲**

የዚሁ ፅሑፍ ዋና መልእክት ከአርእስቱ መላምት ማግኘት እንደሚቻል በቀላሉ መገመት ይቻላል። ታሪክ ማወቅ ስላለፉት ተሞክሮዎቻችን በጥልቀት ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ለወደፊትም ቀናውን መንገድ ለመዳዝና ግባችንን ለመምታትም ጭምር ስለሚያስችለን ነው። በታላቁ የታሪክ ሂደት ታድያ ሐላፊነትን ተሸክሞ ለሚቀጥለው ትውልድ ቅርስን የሚያስተላልፍ ወጣቱ ትውልድ እና ተማሪው ነው። ለወጣቶቹ የታሪክን እውቀት የሚያስጨብጠው ደግሞ ተራማጁና አገር ወዳድ አርበኛ ምሁር ነው። ታሪክ ማለት ግን አፈ-ታሪክ ማለት አይደለም፤ ታሪክን መሠረት በማድረግ ትንታኔዎችና አቃቂሮችን ማቅረብ የሚፈልግ ማንኛውም የተማረ ሰው ወይም ሐቁን አውቀዋለሁ የሚለውን ማንኛውም ግለሰብ ርትዓዊ የሆኑ ደጋፊ ሐሳቦች፡ መረጃዎችና ሰነዶችን ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ይህ ጽሑፍ ብዙ ርእሰ-ነገሮችን ያካተተና ዓበይት ነጥቦችን ያጠናቀረ ስለሆነ የኢትዮጵያ ወጣቶችና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በልዩ ልዩ መድረኮች ይወያዩባቸው ዘንድ ዋና ዋና የውይይት ርእሶችን በቅደም ተከተል አቅርቢያቸዋለሁ፤ ስለሆነም መጀመርያ ታሪክን ላስቀድም።

## የኢትዮጵያ ታሪክ

አንዳንድ የታሪክ ተማራማሪዎች እንደሚሉት የኢትዮጵያ ታሪክ የሚጀምረው ከንግሥተ ሳባ ወይም ከአክሱም ሳይሆን ቀደም ብሎ የተጀመረ ነው። ከአክሱም በፊት ከ 500 እስከ 800 ዓመተ ዓለም (ዓዓ) የየሐ ወይም ዳማት ስልጣኔ ነበር፤ ከዛ በፊት ደግሞ ማለትም 2000 ዓዓ ገደማ የሸክላ ሰሪና ከብት አርቢ ማሕበረሰብ ስልጣኔ እንደነበር ጎበድራ (አክሱም አጠገብ) በተሰኘው ሰፈር በተገኙት የአርክዮሎጂ ቅርሳቅርሶች ለማረጋገጥ ተችሏል፤ ኢትዮጵያ የተባለው ስያሜ የተጀመረው ግን ኢትዮጲስ ፲ኛ በ፲፰፭፮ ከነገሠ ወዲህ ነው፤ ከኢትዮጲስ በፊት አራት ነገሥታት በድምሩ ለመቶ ሃያ ዘጠኝ ዓመታት ነግሰዋል። በዛን ጊዜ ኢትዮጵያ ብሔረ እግአዚ ትባል ነበር። ንግሥተ ሳባ (ማክዳ)ደግሞ ፭፪ኛ ንግሥት ነበረች፤ የነገሰችውም በ1013 ዓዓ ስለነበር የመጀመርያ የኢትዮጵያ መራሔ መንግሥት ልትሆን አትችልም።
የኢትዮጵያ ስልጣኔ በከፍተኛ ደረጃ መንፀባረቅ የጀመረው ደግሞ አክሱም ኃይለኛ መንግሥት ሆኖ ከ ፱ እስከ ፬ ዓመተ ምሕረት (ዓም) ማለትም ዘስካለስ በነገሠ ጊዜና ኢትዮጵያ እንደ ጠንካራ ሃገር መንሰራራት በጀመረችበት ሰዓት ነው። ይኸውም ለ900 መቶ ዓመታት ሳያቋርጥ ኃይለኛ፡ ጠንካራና ባለፀጋ ኢትዮጵያን የመራ መንግሥት ሆኖ በመልከአ ምድር ቀዶ ስፋት ደግሞ የዛሬቱ ኢትዮጵያ፡ ኤርትራ፡ ሰሜን ሱዳን (ኑብያ) እና የመንን ያጠቃለለ ነበር።

የአክሱም ነገሥታት በ፲፪ ሽማግሌ አማካሪዎች ተደግፈው ሕግና ደንብን መሠረት በማድረግ ያስተዳድሩ ነበር እንጂ ፈላጭ ቆራጮች ወይም አምባገነኖች አልነበሩም፤ ነገሥታቱ በተጨማሪ ያለ አማካሪዎቻቸው ፈቃድና ውሳኔ ለልጆቻቸው ስልጣን ማውረስ አይችሉም ነበር። የዚሁ ዓይነት የፖለቲካና ያገዛዝ ስርዓት በተለያዩ የጥንታዊትና መካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያ አንሰራተው በነበሩ የአከባቢ ስርዓቶች ተንፀባርቆ ነበር፤ አሁንም ቢሆን የአክሱም ያገዛዝ ስልት ቅሪት ወይም ውርስ በመላ ኢትዮጵያ አለ ማለት ይቻላል። ለምሳሌ የትግራይ የባይቶ ሽማግሌ ምክር ቤት፤ የኦሮሞ የገዳ ዴሞክራስያዊ ሥርዓት፤ በስድስት ምቅሪጬ የተባሉ አማካሪዎች የተደገፈ የካፋ ንጉሥ ካፊኞ ታቱ፤ ከፍትሕ ጋር የተዛመደ የአኗክ የቅዎር (አኵዶ ከተባለ መለከታዊ ኃይል የፈለቀ) ሥርዓት፤ ከ ፲፪ ነገድ የተውጣጡ የጋራሚሮ (በገናሌ እና ዳዋ ወንዞች መሃል፡ ምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኙ ብሔረሰብ) የምርጫና መስተዳድር ሥርዓት፤ የማስተደዳደርና የማስታረቅ ተቋማት የሆኑትን የጉራጌ የጆካ እና ቂጫ ሥርዓቶች፤ በጠቢብነት፡ ክህሎትና ክብር መስፈርቶችን የተመሰረተ የአፋር የፊማ የአመራር ተቋም፤ መስፈርቶችን የማያሟሉ መሪዎች ደግሞ ከስልጣን

እንዲወርዱ የሚያደርግ ሥርዓት። እነዚህን ስርዓቶች በከፊሉ መጥቀስ ይቻላል። ስርዓቶችና ተቋሞችን በጥልቀት ለማወቅና ጥናትና ምርምር ለማድረግ ለሚፈልጉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሁሉ የአሰፋ ጌትነት Indigenous Institutions and Local Development Initiative: Case Studies of Selected Gurage Areas እና የደጄኔ አረዶ እና ይግረመው አዳል Indigenous Institutions and Good Governance in Ethiopia: Case Studies ፈትሸው በማግኘት ያንብቧቸው።

ከላይ የጠቀስኳቸው ስርዓቶች ምን ያህል የኢትዮጵያ ሕዝብ ስረ-መሠረቱ አንድ እንደሆነ በማያሻማ መልኩ ያሳዩናል፤ ሳናውቃቸው ስንቀር ግን አደጋ ይኖራል፤ ያውም የሚያራርቅና የሚያጋድል፤ ምክንያቱም አንድ የሚያደርጉን ነገሮች ባላወቅነውና ባላሰብነው መንገድ ልንቀብራቸው እንችላለን፤ አላስፈላጊና አግባብነት በሌለው መንገድ የኛን ትተን ከኛ ጋር የማይዛመዱ የምዕራባውያን ስልትና ሥርዓት ከተከተልን ደግሞ ጉዳቱ የባሰ ይሆናል። እንግድያውስ እንዲህ ያለ አደጋ በላያችን ላይ እንዳያንዣብብ ሌላ ተጨማሪ ታሪካዊ ጉዳይ ልጥቀስ።

## የኢትዮጵያ ቁሳቁሳዊ ባህል

ቁሳቁሳዊ ባህልን አስመልክቶ ኢትዮጵያ ሃገራችን እጅግ በጣም ሃብታም ናት፤ ልንኮራም ይገባናል። በሃወልቶችና የውቅር ህንፃዎች የተንፀባረቀው የአክሱም ስነ-ህንፃ በበርካታ የኢትዮጵያ ከፍላተ ሃገራት ተዘርግቷል። የተወሰኑ የታሪክ ጸሐፊዎች የአክሱም ስነ-መንግሥት ካበቃ በኋላ ቁሳቁሳዊ ባህሉም አብሮ እንዳበቃ የጻፉ አሉ። እነዚህ ታሪከኞች ግን እጅጉን ተሳስተዋል። የአክሱም ስልጣኔ እስከ አስረኛው ክፍለ ዘመን ከቀጠለ በኋላ መዳከም አሳይቷል፤ ቅርሱ ግን በላሊበላ ቀጠለ እንጂ አላቋረጠም። አሁን ላሊበላ የምንላት ከተማ ሮሃ ትባል ነበር፤ ከዛም በፊት አደፋ ትባል ነበር፤ አደፋ የኢትዮጵያን ሠራዊት መርቶ (ከወንድሙ ከሴዛና ጋር) ወደ ኑብያ የዘመተ ጀነራል ነው፤ የንጉሥ ኤዛና ወንድም ነው።

የላሊበላ ሥርወ-መንግሥት ዛጔ በመባል ነው የሚታወቀው፤ በአፈ ታሪክ እንደሚባለው ሁሉ ዛጔ የሚል ስያሜ ከ ዘአጉየዬ (አሯሯጠ) የሚል ቃል የፈለቀ ነው የሚሉ አሉ፤ ይህ ግን ስሕተት ነው። ቃሉ ከ ያና እንዳ አቦይ ዘገ (አክሱም አጠገብ የሚገኝ) የተወረሰ ለመሆኑ ብዙ ምንጮች ያመላክታሉ። የመጀመርያ የውቅር ቤተክርስትያን በአደፋ አከባቢ ያሰራ ደግሞ ንጉሥ ላሊበላ ሳይሆን አፄ ካሌብ ነው፤ የቤተክርስትያኑ ስም መስቀለ ከርስቶስ (ቅኔ ማህሌት) ይባላል፡ የሚገኘው ደግሞ በሰቆጣ ነው። እርግጥ በዛጔ ዘመነ መንግሥት በላሊበላ ከተማ ፩፩ የውቅር

ቤተክርስትያናት ሲሰሩ፡ ከላሊበላ ወጣ ብሎ ደግሞ በንጉሥ ይምርሃነ ክርስቶስ የተሰራ አንድ የውቅር ቤተክርስትያን አለ። ሁሉም የውቅር ህንጻዎች በአክሱም ስነ-ህንጻ ዘዴ የተገነቡ ናቸው፤ እንድያውም አንዳንዶቹ (እንደ አማኑኤል፡ ጊዮርጊስ፤ ማርያም ወዘተ) የበርና መስኮት ቅርፃቸው እንዳሉ የአክሱም ሃውልት ራስጌ ናቸው። በተጨማሪ ላሊበላ ውስጥ የሚገኝ አንድ ድልድይ በግራና ቀኙ በትናንሽ የአክሱም ሃዎልቶች ያሸበረቀ ነው።

በጎንደርም በተመሳሳይ መልኩ የአክሱም ስነ-ህንጻ ተንጸባርቋል፤ አፄ ፋሲለደስ (1632-1667) ከመንገሳቸው በፊት፡ በኢትዮጵያ ጥንታዊ ሕግና ሥርዓት መሠረት፡ በቤተክርስትያኑ ቅብአ ንግሥነትን ለመቀበል ወደ አክሱም መሄድ ነበረባቸው። ንጉሡ አክሱም እንደደረሱ የሐወልቶቹንና የማርያም ፅዮን ቤተክርስትያን እፁብ ድንቅ አሰራር ስለመሰጣቸው "ጎንደር ውስጥ ተመሳሳይ ሀንጻ መሥራት አለብኝ" አሉና ወደ ጎንደር እንደተመለሱም ህንጻዎቹን ሲያሰሩ በእያንዳንዱ ግምብ ግድግዳ ላይ ወደ ሰማይ ያነጣጠሩ ትናንሽ ሐወልቶች (ልክ እንደ ማርያም ፅዮን) እንዲኖራቸው አደረጉ። ሁለት መቶ ዓመት ከፋሲለደስ በፊት አፄ ዘርአ ያቆብ (1434-1468) ወደ አክሱም ከሄዱ በኋላ የአክሱምን ስልጣኔና የአገዛዝ ስልት በጥልቀት ይፈትሹና "ያገሬ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ስርዓት እንደገና ማስፃፍ አለብኝ" በሚል ቀናኢ ጉጉት ክብረ መንግሥት የተሰኘውን መጽሐፍ ያስጽፋሉ፤ ከቁሳቁስ ባህል ባሻገር፡ ቀደም ብለን እንዳየነው፡ አፄ ዘርአ ያቆብ በኃይማኖታዊ፡ ሰነልቦናዊና፡ ፖለቲካዊ መስተዳድር ላይ ያተኮሩ ነበር።

ወደ ቁሳቁሳዊ ባህል ከተመለስን ደግሞ በአክሱም ጊዜ የተፈጠሩትን ልዩ ልዩ መሣርያዎች እንደ የሸክላ ድስት፡ማጫድ፡ ማረሻ፡ ወንፊት፡ ምድጃ፡ ወፍጮ፡ መጥረብያ፡ የሸማኔ መሳርያ፡ ስፌድ፡ ብራና፡ ብእርና ቀለም፡ የሙዚቃ መሣርያዎች (ዋሽንት፡መለከት፡ክራር፡ማሲንቆ፡በገና፡ከበሮ) ወዘተ በመላ ኢትዮጵያ ተዘርግተው ይገኛሉ። የሸማኔ የልብስ ምርቶች ከትግራይ እስከ ዶርዜ ሃይዞ በዓይነትም በይዘትም አንድ ናቻው፤ እንደዚሁም ስፌዶች ከትግራይ እስከ ሐረር በዓይነትም በይዘትም ተመሳሳይ ናቸው። አንድ ዓይነት የጥበብ ከህሎት ያለውና አንድ ዓይነት ተመጋጋቢ የሆኑት እሴቶችን የሚጋራ ሕዝብ መጠርያው 'ሕዝብ' እንጂ 'ሕዝቦች' መባል የለበትም፤ ስለሆነም ያሁኑ ስያሜ "የኢትዮጵያ ህዝቦች" የሚለውን ወደ "የኢትዮጵያ ሕዝብ" መቀየር አለበት።

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምራ የተማከለ ያገዛዝ ሥርዓት ፈጥራ ስለነበረች ንጉሡ ወይም ንጉሠ ነገሥቱ በአክሱም ከተቀባና ንግሥነቱን ከተረከበ(ች) በኋላ ምልአተ ሕዝቡ

“የነገሠ ንጉሣችን የወጣችው ፀሐይ ፀሐያችን” በማለት ሕጋዊ እውቅናን ይሰጠዋል/ይሰጣታል (ልብ በሉ፡- አያሌ ሴቶች በኢትዮጵያ ነግሰዋል)። ለዚህም ነው ንጉሡ ለብዙ ምዕተ ዓመታት ያገር አንድነት ሆኖ ያገለገለው፤ ንጉሡ የሾማቸውንም ሳይቀሩ በሕዝብ ተቀባይነት ያገኙ ስለነበር ቋንቋና ብሔር ሳይገድባቸው በሄዱበት ያገለግሉ ነበር። ለምሳሌ በአፄ ሱስንዮስ ጊዜ ቅብአ ክርስቶስ የሚባል ከጎንደር ተሹሞ ትግራይን ያስተዳድር ነበር፡- በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ደግሞ ኃያሉ ራስ ሚካኤል ስሑል ከትግራይ ወደ ጎንደር በመሄድ ይገዙ ነበር። እንዲህ ያለ የፖለቲካ ሥርዓትና እጅግ የመጠቀ ቁሳቁሳዊ ባህል ያዳበረች ኢትዮጵያ ቀጥለን በምናየው ርእሰ ነገር ማለትም ክልልና ብሔር በዘለለ መልኩ ነበር ሕብረተሰቡን ታስተዳድር የነበረችው።

## የክልልና የብሔር ጉዳይ

ኢትዮጵያ ሕብረ-ብሔር ለመሆኗ አንድም ሁለትም የለውም፡- ነገር ግን በዓለም ዙርያ ከጥቂት አገሮች በስተቀረ (ለምሳሌ ጃፓን) ሁሉም አገሮች ሕብረ-ብሔር ናቸው። ሕብረ-ብሔር መሆን ደግሞ ኢትዮጵያ ሃገራችን ከፍተኛ እምቅ ኃይል እንዲኖራትና ሃብታም እንድትሆን ያደርጋታል እንጂ አሉታዊ ክስተቶችን አያመጣባትም። ይኽንን ሃብት በጥንቃቄ ካልተያዘ ግን አደጋ አለው፤ ለምን? ዝርዝሩን እንደሚከተለው ማቅረብ እፈልጋለሁ።

በአፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ካነሳቸው ዓበይት ጥያቄዎች አንዱ የብሔር ጥያቄ ነበር። ተማሪዎቹ (እኔም ጭምር) በደፈናው “የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰንና እስከ መገንጠል” የሚል መርሕ አንግበ ነበር የተንቀሳቀሱት። ነገር ግን ተማሪዎቹ የብሔሮች መብት ለማስጠበቅ መፈክሩን ቢያስተጋቡም ቅሉ የመነጣጠልና የመገነጣጠል አደጋ ሊኖር እንደሚችል ግን አልተገነዘቡም ነበር። ኢሕዴግም ከዛ ስሕተት መማር ስላልቻለ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የብሔር ጥያቄ አጀንዳ (በተለይም የዋለልኝ መኮንን ጽሑፍ እና የስታሊን ርእዮተ-ዓለም ንድፍ) ቆኖናዊ በሆነ መንገድ በመከተልና በግብር በመተርጎም በቋንቋ የተሸነሸኑ የክልል ፈደረሽን ፈጠረ።

የብሔሮች ነፃነት፤ ባህላቸውና ቋንቋቸውን እንዲያበለጽጉና እንድያጎለብቱ ማድረግ እኔ በበኩሌ በማያወላዳ መንገድ የምደግፈው ጉዳይ ነው። ክልሎቹ በቋንቋ መካለላቸው ግን ትክክል አይደለም። የዚሁ ችግር የሚያስከትለው ውጤት ገና ክጅምሩ ከንክኖኝ ስለነበር እአአ በ1995 በጻፍኩት መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ብዬ

ነበር፡- "የክልሎች ራስን በራስ የመወሰን ዕድል የሚደነቅ ነው፤ የመቆራረጡ ውጤት ግን አዲስ የጎሳ የፖለቲካ የንቃተ ሕሊና ማዕበል ከማስከቱሉም በላይ አናሳ ብሔሮች በምጣኔ ሃብትና ፖለቲካ ረገድ ራሳቸውን ማሳደግ የማይችሉበት ሁኔታ ይፈጠርና የኋላ ኋላ ኢትዮጵያውያን ባልተጠበቀው ችግር ውስጥ ሊዋጡ ይችላሉ"። ያው የፈራሁትን ነገር እውን ሆኖ እንደ መጥፎ ሕልም (ቅዠት) እያስበረገገኝ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን ለምን በብሔርና በጎሳ መናቆር ጀመረ? ቀደም ብዬ የጠቀስኳቸውን እሴቶች ወዴት ገቡ? እሴቶቹ አሁንም ቢሆን አሉ፤ ሁላችን እንደምናውቀውና አልፎ አልፎ እንደምናየው ያገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች በጥበብና በብልሃት ግርግሩን ለማርገብ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። ዋናው ችግሩ እኔ እንደሚመስለኝ ግን አሁን ያለው ትውልድ ታሪኩን ስላላወቀውና ከሚለያዩት ባህሎች አንድ የሚያደርጉትን እሴቶችን በቅጡ ስላልተረዳውና ማላመጥም ስላልቻለ: ለኢትዮጵያ ማንነት ሳይሆን ለብሔር ማንነት ቀዳምነት ስለሰጠው ይኸው ብሔር በብሔር ላይ፤ ብሔረሰብ በብሔረሰብ ላይ መተናኮስ: መቧጠጥና: መገዳደል ተጀመረ። ይህ የመናቆርና የግጭት ፖለቲካ ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያልተከሰተ ነው።

ከዚሁ ከጎስ ፖለቲካ ለመውጣት ፍላጎት ካለን ግን መፍትሔው ቀላል ነው። የመጀመርያው መፍትሔ ብሔርን መምረጥ እንደማይቻል ማወቅ ይኖርብናል፤ ይኸንን ምክንያታዊ ወይም ርትዓዊ እሳቤ መጀመርያ ያፈለቅኩት እኔ ነኝ። እአአ በ2005 በጻፍኩት መጣጥፍ ውስጥ እንዲህ ብዬ ነበር፡- "አገር ወዳዱ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የአንድ ብሔር አባል የሆነውን እንዳጋጣሚ መሆኑን፤ ኢትዮጵያዊነት ግን በታሪክ የተገነባ መሆኑን በቅጡ ይገነዘባል። ይህ በቀላል አማርኛ እንዲህ ማለት ነው፡- አንድ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ የትግራይ ተወላጅ፤ የአማራ፤ የኦሮሞ፤ ጉራጌ፤ ሲዳማ ወዘተ አባል ሊሆን የቻለው እንደአጋጣሚ እንጂ ሆን ብሎ በእቅድ ከዚሁ ብሔር ልፈጠር ብሎ በመምረጥ አይደለም። እንዲህ ያለ ክስተት ተሰምቶም ታይቶም አይታወቅም ፡ ለወደፊትም አይኖርም"። የመጣጥፉ አርእስት "ለኢትዮጵያ የሚበጅ የፖለቲካ ስትራተጂ መቀየስ የሁላችን ሐላፊነት ነው" የሚል ሆኖ ከታች በተመለከተው አያያዝ (link) ገብቶ ዝርዝሩን ማንበብ ይቻላል፡- www.africanidea.org/doc5.pdf

ሁለተኛው መፍትሔ ብሔርን በዘለለ መልኩ የኢትዮጵያዊነት ማንነትና ሃገራዊ ስሜት በመያዝና በማቀፍ አብሮ በመዳዝና ክንድ ለክንድ ተያይዞ አገራችንን ወደተሻለ መንገድ መምራት ብቻ ሳይሆን በስርነቀል ለውጥ እንድትበለፅግና

እንድትመጥቅም ጭምር ማድረግ ነው። ሌላ አማራጭ የለም። ኢትዮጵያዊ ስሜትና ማንነት ግን ከሁሉም በላይ ቅድምያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፤ የዛሬ ዘጠኝ ዓመት “ማን ነው ኢትዮጵያዊ” በሚል ርእስ እንዲህ ብዬ ተከራክዬ ነበር፡- “የአንድ ሕዝብ ቅይጥነት: በባህልና ቋንቋ መመሳሰል እና የጋራ ስሞችን መጠቀም ወዘተ ሊንፀባረቅ ይችላል። እነዚህ ሕዝቦች ታድያ በጎሳ፡- በብሔር ወዘተ ራሳቸውን ቢገልጹም ቅሉ የላቀና የጋራ ማንነታቸው ግን አገር-አቀፍ የሆኖውን ኢትዮጵያዊ የሚለውን መለዮ ነው። ለምሳሌ የሰዎች ስም ብንወስድ ብርሃነ (ትግርኛ): ብርሃኔ (አማርኛ): ተስፋይ (ትግርኛ): ተስፋዬ (አማርኛ): አስፍሃ (ትግርኛ): አሰፋ (አማርኛ) ትርጉማቸውና አደማመጣቸው አንድ ነው፤ የሁለቱ ቋንቋዎች መሠረት ደግሞ ግእዝ ነው። ነገር ግን ‘ደስታ ገበረወልድ’ እና ‘ሕይወት ገብረማርያም’ የጎጥ ወይም የጎሳ ማንነታቸው ካልገለጹ በስተቀረ የብዙ ኢትዮጵያውያን የጋራ ስሞች (በተለይም የትግራይ: አማራና ጉራጌ ብሔር ተወላጆች) ስለሆኑ ሃገራዊና አድማሳዊ ባህልን ነው የሚያንፀባርቁት።” የጽሑፉ ይዘት በዝርዝር ለማንበብ ከፈለጉ በ www.africanidea.org/ethiopiawinet.html ላይ ይጫኑ።

ክልሎቹን አስመልክቶ ግን ካለው የአሁኑ የፈደራል አወቃቀር የተቆራኘ ስለሆነ: የፈደራል ሥርዓቱ ደግሞ በኔ እምነት መቀጠል ስላለበት ማሻሻያዎችንና ጥገናዎችን በማድረግ ላሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች እርማቶችን ማድረግ እንችላለን። በኔ በኩል መፍትሔው እንደሚከተለው ነው፡- ክልሎቹ በመጠኑም ቢሆን የብሔሮችን መብት ስላረጋገጡ አሁን በያዙት ቅርጽ ይቀጥሉ፤ ነገር ግን: ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው: በቋንቋ የተካለሉ ራስ ገዞች አንድነታችንን ስላናጉት: የጋራ ማንነታችን የሆነውን ኢትዮጵያዊነትን ደግሞ ስላዳከሙት እያንዳንዱ ክልል (ናይጀርያኖች እንዳደረጉት) ሕብረ ብሔር እንዲሆኑ ማድረግ ነው። በሌላ አነጋገር የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ኢትዮጵያውያን በማንኛውም ክልል እንዲኖሩ: እንዲሰሩ: እንዲነግዱ: እንዲያርሱ: የዜግነት መብታቸውም እንዲጠበቅላቸው ማድረግ በግዚያዊ መልክም ቢሆን የተሻለ መፍትሔ ነው።

## የሕግ የበላይነትን አስመልክቶ

የሕግ የበላይነት ምን ማለት ነው? ሕገ መንግሥቱና ሌሎች የሕግጋት ዘርፎች ማክበርና በነሱ መገዛት ማለት ነው። ሕገ መንግሥቱ ከሁሉ በላይ የላቀ የሕግ ሰነድ ስለሆነ የሃገር ሕግ ይባላል፤ ስለሆነም ሁሉም ዜጋና ሁሉም ባለስልጣን ከሕጉ በላይ መሆን አይችሉም፤ ሕጉ ከነሱ በላይ ነውና። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት አለ የለም? ለሚለው ጥያቄ መልሱ የለም ነው። ቢኖር ኖሮ’ማ አንዳንድ የክልል

ባለስልጣናት “በሕገ-መንግሥቱ አንገዛም” አይሉም ነበር፤ የአንድ ብሔር ተወላጆች በክልላቸው ሲጠቁና ሲገደሉ ዝም ብለው አያዩም ነበር፤ በሶማልያ ክልል እንዳየነው ቤተከርስትያናት አይቃጠሉም ነበር፤ ካህናቱም አረሜናዊ በሆነ መንገድ አይገደሉም ነበር፤ በጣና በለስ የትግራይ ተወላጆች ተገድለው አስከሬናቸው መንገድ ላይ (ልክ ደርግ እንዳደረገው) አይዘረጋም ነበር፤ በደብረ ማርቆስ በረከት ስምኦን አለበት ተብሎ ሆቴሉ አይቃጠልም ነበር፤ በሻሸመኔ አንድ ንፁህ ኢትዮጵያው ዜጋ በሰው-መንጋዎቹ ተዘቅዝቆ አይሰቀልም ነበር ወዘተ ወዘተ፤ ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ እንኳንስ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት አገር ልትሆን ይቅርና፤ የሕግ አልባነት ያጠቃት አገር ሆናለች። የሕግ የበላይነት እንደገና እንድያንሰራራ ከተፈለገ ግን ማእከላዊ የፈደራል መንግሥቱና ጠቅላይ ሚኒስተሩ ከፍተኛ ሐላፊነት በመሸከም ሕግና ፍትሕ በግብር የሚተረጎሙበት መንገድ መቀየስ አለባቸው፤ ሕግጋቱን ማክበርና ማጠንከር አለባቸው።

ለኛ ኢትዮጵያውያን ሕግና ደንብን አስመልክቶ ብርቅ ነገር አይደለም። በአንዳንድ የዓለማችን አከባቢዎች የተለያዩ የሕብረተሰብ አባላት ዋሻ ወስጥ በሚኖርበት ጊዜና ገና የድንጋይ ዘመን መሳርያዎችና ስልቶችን በሚጠቀሙበት ጊዜ የኛ ቅድመ አያቶች ግን፤ ከፍ ብለን እንዳየነው፤ ቅዋመ ሕግና የተለያዩ የመስተዳድር ሕግጋት ፈጥረው ነበር። ይህ ሃብታም ቅርስ በመርሳትና በመዘንጋት አሁን በሕገ አልባነት ስንናቆር በጣም የሚያሳዝን ክስተት ነው፤ ነገር ግን አሁንም ቢሆን አልረፈደም፡ አልመሸም ገና፤ ለሃገር ፍቅርና ለሕዝብ ተቆርቋሪነት ብለን በአንድነት ከተነሳን የሕግ የበላይነትን እንደገና እንዲያንሰራራ ማድረግ እንችላለን። ሕግና ደንብ የሰላም ዋስትና ከመሆናቸውም በላይ እርጋታና ጸጥታም ስለሚያጎናጽፉን ወደ ልማት ጎዳና ለማምራትም አመቺ ሁኔታ ይፈጥሩልናል ማለት ነው። በሕግና በደንድ የሚገዛ ሕዝብ ጨዋ ሕዝብ ነው። ጨዋ ሕዝብ  ማለት ግን ምን ማለት ነው?

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋነት

ይኸንን ርእሰ-ነገር አስመልክቶ ከዚህ ቀደም ከኢትዮጵያ ታሪክና ባህል በማዛመድ መጠነኛ መጣጥፍ አቅርቤ ነበር፤ በዛን ጊዜ ግን በእርግጠኝነት የኢትዮጵያውያን ጨዋነት በከፍተኛ ደረጃ የተንጸባረቀበት ጊዜ ነበር። ወቀቱ የባድመ ጦርነት ጊዜ ነበር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገሩን ድንበርና ሉዓላዊነት ለማስከበር ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ተነሳ፡ መስዋእትነትም ከፈለ፤ በዓድዋ ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው ጣልያንን በመውጋትና በማቸነፍ የሃገራቸውን ድንበርና ሉዓላዊነት እንዳስከበሩ ሁሉ በባድመም አንድ ሕዝብ ሆነው ስለቀረቡ ጨዋነትን በከፍተኛ ደረጃ

አንጸባርቀውታል ማለት ይቻላል። ስለሆነም እኔ እንደማየው ከሆነ ጨዋ ሕዝብ ማለት ለሃገርና ለሕዝብ የሚቆረቆር፤ ለኢትዮጵያ ነፃነት የሚቆም፤ የብሔርና ጎሳ ፖለቲካ የማያራምድ፤ ለውጭ ኃይሎችና ለኢትዮጵያ ጠላቶች የማያጎበድድ፤ ኢትዮጵያ ወደፊት እንድትራመድና እንድትበለፅግ ሌት ተቀን የሚጥር፤ የኢትዮጵያን ስልጣኔና ባህል የሚያንፀባርቁ ቅርሶችን ለመጪው ትውልድ የሚያስተላልፍ እና ለአሁኑ ወጣትና ተማሪ ደግሞ እውቀትና በጎ እሴቶችን የምያሳቅፍ ነው ጨዋ ማለት። ወጣቱም በበኩሉ የነገ አገር መሪ መሆኑን ተገንዝቦ ከአንጋፋው ትወልድ እውቀት: እሴት: ብሂል: ባህል: ታሪካዊ ተመክሮ ወዘተ ለመረከብ ዝግጁ መሆን አለበት፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፈውን ችቦ ደግሞ መሸከም ይኖርበታል። ይህ ለኢትዮጵያ ወጣት ሁሉ የግጥምያ ጥሪ ነው! ነገር ግን አሁንም ቢሆን በጨለማው መሿለክያ ብርሃን የሚያበራ ወጣት ተነስቷል፤ዕድሜ ለኢትዮጵያ ወጣቶች ፈደረሽን ወሰኘ ተሻጋሪው ወጣት በበጎ ፈቃድነት በመነሳሳት በትግራይ በደቡብ እና ሌሎች አከባቢዎች በመሰማራት ችግኝ ተክሏል:ቆሻሻን አፅድቷል: ደም ሳይቀር በእርዳታ መልክ አበርክቷል፤ “እኛ ከተለያዩ ክልሎች ብንመጣም ቅሉ አንድ ሕዝብ ነን” በማለትም ዘምሯል። ይህ የከፍተኛ ጨዋነት ተምሳሌት ነው፤ ለመጪው ትውልድም አርአያ ሆኖ ያገለግላል።

## የኢትዮጵያ ባንዴራ ጉዳይ

የባንዴራው ጉዳይ ከመቸውም ጊዜ አወዛጋቢና አነጋጋሪ ሆኗል። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይም ወጣቱና ተማሪው፤ ስለ ባንዴራው ታሪክ እውቀት ስለሌለው ውዥንብር ውስጥ የገባ ይመስለኛል። አብዛኛው ወጣት የኢትዮጵያ ባንዴራ በኢሕአዴግ እንደተቀየረገና ዝንተ-ዕለት ልሙጥ እንደነበረ የሚመስላቸው አሉ፤ ይህ ግን ስሕተት ነው፤ ስህተቱም የመነጨው ወጣቱ የባንዴራውን ታሪክ ባለማወቁ ነው። የኢትዮጵያ ባንዴራ አመጣጥና አጀማመር አስመልክቶ ቀጥለን እንደምናየው ይሆናል።

መጀመርያ የባንዴራውን ጽንሰ ሐሳብ ያፈለቀውና በተግባር መጠቀም የጀመረው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ነው። ነገር ግን ቤተክርስትያኑ የዓለማዊ መንግሥት ሰንደቅ ለማውለብለብ ሳይሆን ከሰባቱ የቀስተደመና ቀለሞች ደምቀው የሚታዩትን አረንጓዴ:ብጫ:ቀይ (አብቀ) በመምረጥና እግዚአብሔር ለኖህ የገባለትን ቃል ኪዳን (ዳግመኛ ዓለምን በውሃ እንዳያጥለቀልቀው) በመቀበል ነው አብቀ በየበተክርስትያኑ እንዲቀቡ የተደረጉት። የጥንት የኢትዮጵያ ነገሥታት ደግሞ የ አብቀ ሃይማኖታዊ ይዘት እንዳለ ሆኖ የዓለማዊ ሰንደቅ ወይም አርማ አድርገው

መጠቀም ጀመሩ። ነገር ግን በዛን ጊዜ ሦስት የተለያዩ አብቀ ጨርቆች (pennants) በአንድ ምሰሶ የሚያውለበልቡ እንጂ በአንድ ጨርቅ የተጣመሩ አብቀ አልነበሩም። ከዚህ በኋላ አንድ አራት ማእዘን ቀይ ባንዴራ ለመጀመርያ ጊዜ እንዲውለበለብ የተደረገው በአውሳ (ዓፋር) ባለሥልጣናት ትእዛዝ በ ፩፮ኛ ክፍለዘመን ነው፤ ቀጥሎም በ፩፯ኛ ክፍለዘመን ሦስቱ ቀለማት ቀይ፡ ብጫ፤ አረንጓዴ (ቀብአ) ከአውሳ አልፎ ወደ ሌላ የኢትዮጵያ ክፍላተ-ግዛቶች ተዛመተ። ቀይ ከላይ፡ አረንጓዴ ከታች፡ብጫ ከመሃል በአግድም የተሰለፉበት ባንዴራም ነበር።

ኢትዮጵያ ለመጀመርያ ጊዜ የይፋ መንግሥታዊና ሃገራዊ ባንዴራ መጠቀም የጀመረችው ግን ከዓድዋ ጦርነት በኋላ እአአ በ1897 ሆኖ ይህ ባንዴራ ሦስቱ ቀለማትን በአንድ ጨርቅ ያጣመረ ነበር፤ አረንጓዴ ከላይ ብጫ ከመሃል ቀይ ከታች ሆኖ በመሃል ደግሞ ዘውድ የጫነ፡ ባንዴራ በመስቀል ላይ ያነገበ የይሁዳ አንበሳ አለበት። ይህ ባንዴራ ለ፯፯ ዓመታት ከ 1897 እስከ 1974 ዓም በአፄ ምንሊክ፡ በአፄ ኢያሱ ፭ኛ (ልጅ ኢያሱ) እና በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥታት የኢትዮጵያ ባንዴራ ሆኖ አገልግሏል፤ በአፄ ምንሊክ ጊዜ ባንዴራው መሃል ብጫው ላይ 'ም' (ምንሊክ) ፊደል ተጨምሮበት ነበር።

ደርግ በትረ-ሥልጣኑን ከጨበጠ በኋላ ከ1974 እስከ 1975 ባንዴራው ቀጥሏል፤ የተቀየረ ነገር ቢኖር አንበሳው ከመስቀል ይልቅ ጦር (ቀስት) እንዲያነግብ ነበር የተደረገው። ከ1975 እስከ 1987 ደግሞ ደርግ አንበሳውን ከናካቴው በማውጣት ባንዴራውን አብቀ ብቻ እንዲሆን አድርጎ ነበር፤ ክ1987 እስከ 1991 ደርግ ባንዴራው መሃል ላይ የሾሻሊስት አርማ የሆነውን በአረንጓዴ ጨረሮች የተከበበ ዙርያው ቀይ የሆነ ብጫ ኮከብ እንዲለጠፍበት አድርጎ ነበር። ደርግ ወድቆ ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ፡ በሽግግሩ ጊዜ (1991-1996) ደርግ ከሥልጣን እስከ ተወገደበት ግዜ የደርግ አርማ ወጥቶ አብቀ በቻ እንዲሆን ተደርጎ ነበር፤ ይህ ባንዴራ ለአንድ ስምንት ወር ብቻ ከቀጠለ በኋላና ኢትዮጵያ ፈደራል ዴሞክራቲክ ሪፓብሊክ ከተባለች በኋላ እአአ በጥቅምት 31 1995 በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፫ መሠረት ጨረር ያለበት ሰማያዊ ኮከብ ተጨመረበት።

ከላይ በዝርዝር እንደተቀመጠ ሁሉ የተለያዩ መንግሥታት ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ አንበሳ ወይም ፊደል፤ አርማ ወይም ኮከብ በባንዴራው ላይ ጨመሩበት እንጂ ባንዴራውን አልቀየሩትም፡ ለመቶ ሃያ አንድ ዓመታት አብቀ ሆኖ ቀጥሏል። የባንዴራው ታሪክ ያላወቁ ኢትዮጵያውያን ግን ባንዴራው ምንጊዜም ልሙጥ እንደነበረ ስለሚመስላቸው ኢሕአዴግ ለጨመረበት ኮከብ ክፉኛ ሲቃወሙ

ይታያሉ። በኔ አመለካከት አሁንም ቢሆን የባንዴራው ገጽታን አስመልክቶ ለውጥ ያስፈለጋል ከተባለ ወይም አብቀ ብቻ ይሁን ከተባለ በሕገመንግሥቱ ወይም በ ውሳኔ-ሕዝብ (ረፈረንደም) እንጂ በሁካታና በግርግር መሆን የለበትም፤ እዚሁ መጣጥፍ ውስጥ በግልጽ እንደተቀመጠው ሁሉ ኢትዮጵያ ሃገራችን ከመቸውም ጊዜ የሕግ የበላይነት ያስፈልጋታል።

ለማጠቃለል ያህል የዛሬ ሁለት ዓመት "ተኝቻለሁ እንጂ አልሞትኩም" በሚል ርእስ የጻፍኩት ድርሰት ለወጣቱ ትውልድ ማካፈል እፈልጋለሁ፤ በጽሑፉ ላይ ኢትዮጵያ ራሷ እንደ ህያው ሰውና ራሷ እንደምትናገር አድርጌ ነው ያቀረብኳት፤ እንዲህም ትላለች፡- "ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ልጆቼ ታሪክን መሠረት በማድረግ ምክር ልለግስላችሁ እፈልጋለሁ። ይህም የምልበት ምክንያት ደግሞ ያሁኑ ትውልድ ታሪኩን የዘነጋ ስለመሰለኝ ነው፤ እንድያውም የኔን የናቱን ስም ከመጥራት ይልቅ የጎጥና የጎሳ ልዕልና ማሞገስ፡ ከዛም አልፎ የጎሳ ጥላቻ መሰንዘር ስለጀመረ ነው። ይህ አዲስ የዘቀጠ ፖለቲካ የኔን ባህርይ አያንፀባርቅም። ከሁሉ ያሳዘነኝ ግን አንዳንድ ከአብራኬ የወጡ ልሂቃንና ምሁራን የወጣቱ ትውልድ አካሄድ ስሕተት መሆኑን እያወቁ ሆን ብለው ብሔር ከብሔር፤ ጎሳ ከጎሳ በማናቆርና በማጋጨት ሊበጠብጡኝ፡ ሊያሳምሙኝ፡ከቻሉም ሊገድሉኝ እየመከሩ መሆናቸውን ስለተረዳሁና በዚሁ እኩይ ተግባራቸውም የጦፈ እንቅስቃሴ ማካሄዳቸውን ስለተገነዘብኩ ነው። ነገር ግን እነዚህ ለባአዕዳን የተገዙ ኃይሎች ወድያና ወዲህ ቢራወጡና ቢንቀሳቀሱም እኔን በመጡኑ ለመጉዳት ካልሆነ በስተቀረ ለሞት ሊዳርጉኝ አይችሉም። እኔ እንደሆነ ፍንክች አልልም፡ አልሰበርም፡ አልበተንም፡ አልሞትም። እነዚህ እርጉማን አላወቁትም እንጂ እኔ ለሚቀጥሉት የኢትዮጵያ ትውልዶች በቀጣይነት ለመንከባከብና ለማስተናገድ ፈር ለማስያዝም ጭምር ሐላፊነት ስላለብኝ፡ የግዴታ ሁሉንም ችግር በመቋቋም እስከ መጨረሻ እዘልቀዋለሁ። አበው ያሉትን ትዝ ይላችሁ እንደሆነ "እግዚኦ ኩነኔከ ሃቦ ለንጉሥ፡ ወጽድቁከኒ ለወልደ ንጉሥ" ነውና እኔም እንደ ንጉሡ (ባሁኑ ጊዜ የመንግሥት መሪ) ሸክሙና ኃላፊነቱ የኔ ነው፤ ኩነኔውን (ሸክሙን) እቀበለዋለሁ። በጣም ከፋ ከተባለ ደግሞ "ፅድቁ ቀርቶ በውጉ በኮነነኝ" ማለቴ አይቀርም። ነገር ግን በልጆቼ ስለምተማመን ይኸን ያህል ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር አይደለም በማለት ደግሞ ራሴን አጽናናለሁ።" ዝረዝሩን በ www.africanidea.org/doc5.pdf ተመልከት።

ወጣቶች የእናት አገራችሁ ጥሪ ተቀበሉ፤ ወጣቶች ታሪካችሁን ማወቅ አለባችሁ፤ ታሪካችሁን ካወቃችሁ በኋላ ደግሞ ደም ግባታችሁ ብቻ ሳይሆን ምን ያህል ግዙፉ የኢትዮጵያ የጋራ መገለጫና ማንነት እንዳላችሁ ትገነዘባላችሁ፤ ከጠባብ የጎጥና ጎሳ

አመለካከት ነጻ ወጥታችሁም አነሰ ከተባለ የኢትዮጵያ ሃገራዊ ማንነት፤ ጎለመሰ ከተባለ የአፍሪቃ ኩራትና አመለካከት፤ በዛ ከተባለ ደግሞ የዓለም አቀፍ ባሕረ ሐሳብ ወይም ርዕዮተ ዓለም አስተሳሰብ ታንፃላችሁ፤ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በትምህርት ገበታ የተሰማራችሁ ተማሪዎች ደግሞ የኢትዮጵያን ታሪክ አስመልክቶ ሰፊ ጥናታዊ ምርምር ማካሄድ አለባችሁ። የታሪክ ሰነዶችን ባገላበጣችሁ ጊዜ ደግሞ ምን ያህል አንድ ሕዝብ መሆናችሁን ትገነዘባላችሁ።

**የደራሲውና የአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (አ.ል.ት.ተ.) በዓለም አቀፍ የማሰብና የመመራመር ባለቤትነት በሕግ የተደነገገ ነው።2010 ዓም። All Rights Reserved © Copyright of the Intellectual Property of the Institute of Development and Education for Africa (IDEA) 2018**
**For educational and constructive feedback Dr. Ghelawdewos Araia can be contacted via dr.garaia@africanidea.org**